# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ ሠራተኛ፡ ገበሬ፡ ነጋዴ፡ ወታደር ፣ ምሁር መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም ::

---

ቁጥር 13 3.3.67


## ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች

ሕዝባዊ መንግስት ተቋቁሞ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ስራ ላይ ሳይውሉ ከትግሉ ሜዳ ፈቀቀ አንልም፣ እድገት በህብረት የእውቀትና የስራ መዘቻ በተሰኘውም የወታደራዊው ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ፕሮግራም አንሳተፍም ከሚል ውሳኔ ላይ መድረሳችሁና ከመካከላችሁም ብዙዎቹ በየብሄራቸውና በየክፍለሀገራቸው በመካሄድ ላይ ካሉት የነፃነት እንቅስቃሴዎች ጋር በመቀላቀል አብሮ በመሰለፍ ለሙሉና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ለመታገል መቁረጣቸው በመሰረቱ የሚደገፍና የሰፊውን ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴ ወደፊት የሚያራምድ ነው :: ሆኖም ትግሉን በሚገባ ለመቀጠል የወሰዳችሁት እርምጃ ወደ ትክክለኛ ግቡ እንዲያ ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች ተራማጆች ሊያስቡባቸው የሚገቡ አንዳንድ ጉዳዮች መኖራቸውን ልናስታውስ እንወዳለን ::

በመጀመሪያ ነገር ለመታገል ብላችሁ ከተነሳችሁ ሁላችሁም ጊዜአችሁን በትግል ላይ ማዋል ይገባችኋል :: አንዳንዶቻችሁ ወደ የገጠሩ ተሰማርታችሁ የትግል ግዴታችሁን ስትፈጽሙ ብዙዎቹ ያለምንም ስራ በየከተማው ውስጥ ዝም ብለው ሲንከራተቱ ተራማጆችን በጠቅላላው ከማስወቀሱም ሌላ ለወላጆችና ለህብረተሰቡም ምህረት የሌለው ሸክም ይሆናል :: ስለዚህ በየገጠሩ ሄደው ከሰፊው ሕዝብ ጋር ለመሰለፍ የማይቻላቸው ተማሪዎች በየከተማው ከሰራተኛውና ከሌላው የሰፊው ሕዝብ ክፍል ጋር ለመዋሃድና ለመደራጀት መሞከር ይገባቸዋል :: በጠቅላላውም በየከተማውና በየገጠሩ የምትፈጽሟቸው የትግል ተግባሮች ተፈላጊውን ውጤት እንዲያስገኙ በአጠቃላይና በተቀናበረ መንገድ መመራት ይኖርባቸዋል፣ በግለሰብ ወይንም በትናንሽ ቡድኖች ደረጃ ተወስነው መቅረት አይገባቸውም ::

ሁለተኛ፣ በየከተማውና በየገጠሩ የምታካሄዱትን ትግል ለማቀነባበር ድርጅታዊ አንድነታችሁን መጠበቅ ያስፈልጋል :: ይህም ማለት በምስጢር ብቻ እንኳን ቢሆን ማህበራችሁ ስራውን መቀጠል አለበት፣ ጋዜጣችሁም በየጊዜው መውጣት አለበት ማለት ነው :: ማህበራችሁ ስራውን ከቀጠለና ጋዜጣችሁም መውጣቱን ከቀጠለ በልዩ ልዩ ክፍለሃገሮች የሚታገሉትን ተማሪዎች እርምጃ ለማቀነባበር የትግል ዜናዎችን በመለዋወጥ የታጋዮችን ሞራል ለማጠንከር፣ ጠቅላላ የትግል መስመራችሁንና የትግል አንድነታችሁን ለመጠበቅ ይረዳችኋል :: በግለሰብና በጥቃቅን ቡድን ደረጃ መታገልን ከመረጣችሁ ሃይላችሁ ተበታትኖ ተውጣችሁ ልትቀሩ እንደምትችሉ ማስታወስ ይጠቅማል :: ከሁሉ አስቀድሞ ትግላችሁ ፀረፊውዳል ፀረኢምፔሪያሊስት ፀረጭቆና /ሰብአዊና ብሄራዊ/ መሆኑን ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልጋል :: ይህ ከሆነ ምንም እንኳን ብዙ የሃሳብ ልዩነት በመካከላችሁ ቢኖር የአንድነታችሁን መሰረት በግልፅ ለመወሰንና ድርጅታዊ አንድነታችሁንና ጥንካሬአችሁን ለመጠበቅ ትችላላችሁ ::

ያሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ የተማሪውን ድርጅታዊና የትግል አንድነት ይጠይቃል :: እስካሁን ድረስ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውስጥ ትልቅ ሃይል መሆናቸውን በተግባር ገልፀዋል :: ከዚህ በፊት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያበቃችሁ ድርጅታዊ አንድነታችሁ አሁን በጣም የተዳከመ ይመስላል :: እዚህ ላይ ልናስታውሳችሁ የምንፈቅደው የጨቋኝ መደቦች መሳሪያ የነበረው ሰራዊት እንኳን በመካከሉ ያለውን ልዩነት ለጊዜው ጋብ አድርጎ የመንግስትን ስልጣን ጨብጦ ፀረሕዝብ አስተዳደርን ለመመስረት ሲፍጨረጨር፣ እናንተ ፀረኢምፔሪያሊስትና ፀረፊውዳል የሆናችሁ ምሁራን ደግሞ ከዚህ የበለጠና የተቀደሰ የአንድነት መሰረት እንዳላችሁ መሳት አይቻልም :: ልትጠቀሙበት ይገባችኋል :: በመካከላችሁ የሃሳብ ልዩነት አሁንም አለ፣ ወደፊትም ይኖራል :: ነገር ግን የዚህ ልዩነት መሰረት ከአንድነታችሁ መሰረት ማነሱን ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል ::

አሁን ለጊዜው በመካከላችሁ ልዩነት ካመጡት ጥያቄዎች አንዱ የብሄሮች ጥያቄ መሆኑ ይታመናል ። የብሄሮች ጉዳይ በመሰረቱ ከባድና አጨቃጫቂ ለመሆኑ በታሪክ ተደጋግሞ የተመሰከረ ነው ። ስለዚህ ይህ ጥያቄ በጥንቃቄና በረጋ መንፈስ መቅረብ ያስፈልገዋል ። የብሄሮች ጥያቄ ክርክር ብዙ ጊዜ ስሜት የመቀስቀስ ዝንባሌ ስላለው ተከራካሪዎቹ በስሜታቸው ብቻ እንዳይመሩ መጠንቀቅ ያሻል ። በመሰረቱ አሁን ባገራችን እንደሚታየው በእውነተኛ እኩልነት አብሮ ለመኖር በመፈቃቀድና በወንድማማችነት ስሜት ላይ ያልተመሰረተ በሃይል የተገነባ "የብሄሮች አንድነት" የስሙ ተቃራኒ የሆነ የፌዝ አንድነት መሆኑን ታውቃላችሁ ። ይህ የፌዝ አንድነት ፈርሶ እውነተኛ የብሄሮች አንድነት እንዲገነባ እያንዳንዱ ተራማጅ ኢትዮጵያዊ ጥረት ለማድረግ ግዴታ አለበት ። ይህም ጥረት በትክክል በተግባር ሊገለጽ የሚችለው የገዥው ብሄር አባሎች የብሄራቸውን የበላይነት ስሜት /ሾቪኒዝም/ በመቃወም፤ የተጨቋኝ ብሄሮችም አባሎች የየብሄራቸው ጠባብ ብሄረኛነት ዝንባሌ/ናሮ ናሽናሊዝም/ በመቃወም፤ ሁለቱም ወገኖች ባንድነት ለብሄሮች እኩልነትና እያንዳንዱ ብሄር የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እንዲከበር ሲታገሉ ነው ።

የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ይህን ትክክለኛ አቋም በመውሰድ በተግባር መግለጽ ይኖርባቸዋል ። የተጨቋኝ ብሄሮች አባሎች በየብሄራቸው የትግል እንቅስቃሴ መሰማራታቸው የኢትዮጵያን ሕዝቦች የነፃነት እንቅስቃሴ የሚያፋፍምና ወደፊት የሚያራምድ ነው ። ነገር ግን ድርጊታቸው ሁሉ የተሻለ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የየተጨቋኙ ብሄር ትግል ሲጠቃለልና ከጠቅላላው የሰፊው ሕዝብ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረፊውዳል ትግል ጋር ሲቀነባበር መሆኑን አጥብቆ ማሰብ ያስፈልጋል ።

በመጨረሻም በድጋሚ ልናስታውሳችሁ የምንፈልገው የፖለቲካ ድርጅቶች ባልጠነከሩበት በአሁኑ ጊዜ ፋሽስታዊ አገዛዝን ለመቃወም የተማሪዎች የትግልና የድርጅት አንድነት አስፈላጊ መሆኑን ነው ። ያንድነታችሁን መሰረት በትክክል ባለመረዳት ድርጅታችሁ ቢፈርስና ሃይላችሁ ቢደክም የሚጠቀመው "የተማሪ ነገር ድሮውንስ የልጅ ነገር አይደል" እያለ የሚያፌዝባችሁ የጠላት ወገን ብቻ ነው ። ስለዚህ የትግል አንድነታችሁንና ድርጅታችሁን ማጠንከር ያስፈልጋል ። በውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ከሚገኙትም ማህበራትና ኢትዮጵያውያን ተራማጆች ጋር አንድነታችሁን በማጠንከር ትግሉን መቀጠልና ማፋፋም ነው ።

የተማሪ ማህበራት ከሰፊው ሕዝብ ጋር
ይጠንከሩ
የትግልና የድርጅት አንድነት ይዳብር ።

## መሰረታዊ ለውጥ፡ ምን? መቼ? እንዴት?

ለውጥ ዛሬ በሁላችንም ዘንድ የተለመደ ቃል ነው፤ ረዘም ላለ ጊዜ የብዙዎቻችን ምኞት እንደ ነበር ባለፈው የካቲትና ከዚያም ወዲህ ተደጋግሞ ታይቶአል ። ለውጥን ፊት ለፊት መቃወም የሚፈልጉት በጣም ጥቂቶች ሲሆኑ የቀረው ሁሉ የለውጥ ደጋፊ ነው ። ብዙዎቻችን እምንለያየው ግን ምን አይነት ለውጥ እሚለው ጥያቄ ላይ ነው ።

መሰረታዊ ለውጥ በርከት ካሉ አመታት ጀምሮ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራትና ባንዳንድ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች አካባቢ ሲሰማ ቆይቶአል ። በሌላ በኩል ደግሞ መጠነኛ ጥገና ቢደረግ አስተዳደሩ ቢሻሻል የሰፊው ሕዝብ መብት ሊከበርና ኑሮውም ሊሻሻል ይችላል የሚል ነፋስ ሲነፍስ ነበር ።

በአገሪቱ ላይ አንሰራፍቶ መላውን ሕዝብ ሲጨቁንና ሲበዘብዝ የኖረው በኢምፔሪያሊዝም ስር የነበረው የመሳፍንት ስርአት የአገሪቱን የኢኮኖሚ አቋም ጨርሶ አበላሸ፤ የጥቂት ሃብታሞችን ጥቅምና ደህንነት ብቻ በመጠበቅ ሰፊውን ሕዝብ በረሃብ መቅሰፍት አስመታው ። ከየካቲት 66 ወዲህ የመሰረታዊ ለውጥ ጥያቄ በመላ ኢትዮጵያ እንዳስተጋባ ነው ። መሰረታዊ ለውጥ ዋና የጊዜው ጥሪ ነው ለማለት ይቻላል ።

ታዲያ መሰረታዊ ለውጥ በርግጥ ምንድነው? መሰረታዊ ለውጥ ምን እንደሆነ በትክክል መረዳት ያስፈልጋል ። መሰረታዊ ለውጥ ሲባል አንዱን አምባገነን የጭቆና አገዛዝ በሌላ አምባገነን የጭቆና አገዛዝ መተካት አይደለም፤ ጌታ የመቀያየር ጉዳይ ሊሆን አይችልም ። በአጠቃላይ አነጋገር መሰረታዊ ለውጥ ሲባል በጨቋኝና በተጨቋኝ በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች መካከል ያለውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግንኙነት ሙልጭ አድርጎ አፍርሶ ሌላ አዲስ ግንኙነት መመስረት ማለት ነው፤ የተለመዱት የበዝባዥና የጭቆና መሳሪያዎች መፍረስና መንኮታኮት ማለት ነው፤ በባለመሬትና በጭሰኛ በላብአደሩና በከበርቴው መካከል ያለውን የተዛባና አድሃሪ ግንኙነት መፋቅና የሰፊውን ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚያስከብርና የሚጠብቅ አዲስ ግንኙነት መመስረት ማለት ነው፤ የፖለቲካ ስልጣንን ከጥቂት መሳፍንትና መኳንንት እጅ ማስገባት ማለት ነው ። መሰረታዊ ለውጥ የሁሉም ዜጋ እኩልነት መደብ ብሄር ጾታና እምነት ሳይለይ በትክክል የሚጠበቅበት የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቋም መመስረት ማለት ነው ። መሰረታዊ ለውጥ ከዚህ ያነሰ ሊሆን አይችልም ።

በቁጥር በጣም ያነሱ የገዥ መደብ አባሎች በብዙ ሚልዮን የሚቆጠረውን ሕዝብ የስራ ፍሬ በመግፈፍ የራሳቸውን ጥቅም ያካብታሉ፤ በርካታው ለፍቶአደር ሕዝብ ሰርቶ ያመረተውን እየተገፈፈ በችግር አለንጋ ይገረፋል ። ገበሬው —የገጠር ሕዝብ— በጣም ወደሃላ በቀሩ የእርሻ መሳሪያዎች አርሶ ያመረተውን ሰብል ግማሹን ያህል ለባለመሬቱ አሳልፎ እንዲሰጥ ይገደዳል ። ላብአደሩም ለፍቶ የሚያፈራውን የጉልበቱን ፍሬ አይጠቀምበትም፤ አብዛኛው እጅ ለከበርቴው ይሄዳል፤ ላብአደሩም ለፍቶ የሚያፈራውን የጉልበቱን ፍሬ አይጠቀምበትም፤ አብዛኛው እጅ ለከበርቴው ይሄዳል፤ ላብአደሩ እንዳይሞት ያህል ብቻ ከጉልበቱ ፍሬ በደሞዝ መልክ ጥቂት ይወረወርለታል ።

በአነስተኛ ንግድና በልዩ ልዩ የእጅ ስራ ዘርፎች የሚተዳደረው ንኡስ ከበርቴና ከተማዎችን ያስጨነቀው የስራአጥ ሰራዊትም ብዚህ በተዳፈነ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለአንዳች መተማመኛ የሚንገላወድ ሕዝብ ነው ። የነዚህ ሁሉ በዝባዥ የስርአተማህበሩ የበላይ ተጠቃሚዎች የሆኑት መሳፍንት መኳንንት ጥገኛ ከበርቴዎችና የውጭ ከበርቴዎች ናቸው ። ስለዚህ የለውጡ ዋና አላማ በነዚህ ተጠቃሚዎችና በተበዝባዡ ሰፊ ሕዝብ መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት መቀየር ነው፤ አሁን በሰፊው ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተጫነውን የጭቆና ቀንበር አውዘግዝጎ መጣል ነው ።

እነዚህንም የሰፊው ሕዝብ ጠላቶች በጠቅላላ መልክ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ብለን እናቀርባቸዋለን ። የፊውዳሊዝም /ባላባታዊ ስርአት/ ዋናው መሰረቱ መሬት ሲሆን የባለርስትና የጭሰኛ ግንኙነት ካልተወገደና የመሬት ይዞታ ከስረመሰረቱ ካልተለወጠ በስተቀር በቀላሉ ሊጠፋ የሚችል አይደለም ። ፊውዳሊዝም ለረጅም ጊዜ አንሰራፍቶ በቆየበት እንደኢትዮጵያ ባለው አገር ውስጥ ከንጉሱና ከመሳፍንቱ እጅ ስልጣንን በመውሰድ ብቻ ፊውዳሊዝምን /ባላባታዊ ስርአትን/ እንደመሰሳለን ማለቱ ዘበት ነው ።

የስርአቱ መጠበቂያ መሳሪያ የሆነው የቁጥር ወታደር ለጊዜው ቢከዳቸውም የኢኮኖሚ ሃይላቸው እስካልተደመሰሰ ድረስ ባለመሬቶች ጽኑ ትግል ማድረጋቸውና መልሰው ስልጣን መጨበጣቸው አይቀርም ። በእነርሱ ላይ የሚነሳው የሕዝብ አመጽ የከበርቴውንም ክፍል ስለሚያሰጋው በተለይም በጥቅምና በልዩ ልዩ ዘዴ የተዛመዱአቸው የውጭ ከበርቴዎች በሰፊው ሕዝብ ላይ ጦርነት ማወጃቸው እሙን ነው ።

ስለዚህ ማናቸውም የሰፊው ሕዝብ ወገን የሆነ ለውጥ ፈላጊ እነዚህን ሁለት የሕዝብ ጠላቶች — ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም — ከሚፈለገው ለውጥ ጋር አያይዞ መመልከት ይኖርበታል፣ የነርሱን ብርታትና ድካም ከሰፊው ሕዝብ ብርታትና ድካም ጋር በትክክል ማመዛዘን ይኖርበታል ።

አገራችን ያለችበት ሁኔታ ሲታይ ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅም እውነተኛ ለውጥ በባላባታዊ ስርአትና በኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚደረግ ቆራጥ ዘመቻ ነው ። የሰፊው ሕዝብ ሃይል እነዚህን ሁለት ጠላቶች በአንድነት መምታት አለበት፣ ሁለቱንም በሃይል በመደምሰስ በሕዝቡ ላይ ያላቸውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተጽእኖ ጨርሶ ማጥፋት አለበት፣ መሬትን ወደሕዝብ መልሶ በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና የኢንዱስትሪና የንግድ ድርጅቶች ወርሶ ከኢምፔሪያሊስት ተጽእኖ ነጻ የሆነ ብሄራዊ ኢኮኖሚ መገንባት አለበት ። ይህን የማያደርግ ለውጥ ዘላቂነት የለውም፣ እግሩ አይደርስም፣ ተመልሶ እነርሱው እጅ መግባት ይሆናል ።

ከየካቲት ወር ጀምሮ በተፋፋመው የሕዝብ እንቅስቃሴ የተገኘውን የለውጥ ፍሬ የቀማው በጥቂት ሴረኞች መኮንኖች የሚመራው ወታደራዊ ደርግ መሰረታዊ ለውጥ እንዳመጣ አድርጎ ራሱን በመቁጠር በየእለቱ የሚያደርገውን ፍሬቢስ ድንፋታ እንሰማለን ። የወታደራዊውን ደርግ የስራ ክንውን ስንመለከት አንዳንድ ተነጣላ ድርጊቶችን ከመፈፀምና ውጤቱ አጠራጣሪ የሆነውን ዘመቻ ከማወጅ በስተቀር ምንም የሚጨበጥ ፍሬ አይታይም፣ ይህንንም አተኩሮ ለተመለከተው ምርጦቹ መሰረታዊ ለውጥ እንዳይደረግ የሚከላከሉ የእውነተኛ ለውጥ እንቅፋት መሆናቸውን በግልጥ ያሳያል ።

መሰረታዊ ለውጥ ሊያስገኘው የሚችል አንዳችም እርምጃ አልተወሰደ፣ ንጉሱ ጥቂት መሳፍንትና ባለስልጣኖች ከመታሰራቸው በስተቀር ባላባታዊ ስርአቱ እንዳለ ተትቶአል ። ጭሰኛው ገበሬም ለባለመሬቱ እንደተለመደው እንዲገብር ታዞአል ። የውጭ ከበርቴዎችም እንደልባቸው የሰብአደሩን ጉልበት እንዲበዘብዙ ተፈቅዶላቸዋል ። እንዲያውም በምርጦቹ የሚነዳው ደርግ/የወታደር መንግስት/ እውነተኛ ለውጥ ፈላጊዎችን የለውጥን አፈቀላጤዎች ትንፋሽና እንቅስቃሴ ለማፈን የሚያደርገው ጥረት ቀላል አይደለም ።

ባላባታዊው ስርአት የምርት ሃይሎችና ዘዴዎች እንዳይስፋፉ ወደኋላ በመጎተቱ የእርሻ መሬቶችን በሙሉ በጥቂት ባለመሬቶች እጅ አጠራቅሞ የአርሶበሉውን ገበሬ ጉልበት በመበዝበዝ በአገሪቱ ውስጥ አንዳንድ አነስተኛ እንዱስትሪዎች ቢቋቋሙና ንግዱ በመጠኑ መንቀሳቀስ ቢጀምርም ከውጭና ከውስጥ ከበርቴዎች ጋር በመሻረክና የፖለቲካ ጥላ በመስጠት ሰፊውን ሕዝብ ምን ያህል ሲበድለው እንደቆየ ከላይ ለመጥቀስ ሞክረናል ። ይኸው ባላባታዊ ኢኮኖሚ ዛሬ [illegible] ተናግቶአል፣ በአዲስ ዘዴና በተሻሻለ የምርት ግንኙነት ካልሆነ በስተቀር እንደበፊቱ ሊቀጥል እንደማይችል በግልጥ ይታያል ። ልዩ ልዩ ምክንያት ሊሰጠው ቢሞከርም አገሪቱን ያጥለቀለቀው ረሃብ የባላባታዊው ኢኮኖሚ ውድቀት ምልክት ነው፣ የኢኮኖሚው ውድቀት ውጤት ነው ። እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ሊፈታ የሚችለው መሰረታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ለውጥ በማድረግ ብቻ ሲሆን ይህን ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የዚህ ለውጥ ባለቤት የሆነው ሰፊው ሕዝብ ብቻ ነው ።

ሰብአደሩ ጭሰኛውና ድሃው ገበሬ ተማሪው መምህሩ ምሁሩ ወታደሩ ዝቅተኛው ነግዶ አዳሪ ወዘተ. እነዚህ ሁሉ በለውጡ እንቅስቃሴ ውስጥ በሙሉ ልብ መሰለፍ አለባቸው ። መሰረታዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው በዚህ አይነት መንገድ ብቻ ነው እንጂ እፍኝ በማይሞሉ ሴረኞች ወይም በጠመንጃና በሳንጃ በማስፈራራትና በማስገደድ አይደለም ። ይህ ደህና [illegible]-ተደርጎ መታወቅ አለበት ።

ካለፈው የካቲት ጀምሮ ሲካሄድ የቆየውና አሁንም በመቀጠል ላይ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የአጠቃላይና የጠንካራ ድርጅትን አስፈላጊነት በጉልህ አሳይቶአል ። ሰፊው ሕዝብ ልዩ ልዩ የሙያና የመረዳጃ ድርጅቶች አሉት፣ በእነዚህም አማካይነት ውስጥ ውስጡን ሲታገል የቆየ ቢሆንም በእንደዚህ አይነት ድርጅት የመንግስት ስልጣን መያዝ አለመቻሉን የየካቲቱ እንቅስቃሴ በይፋ አስረድቶአል ። የትግሉን ፍሬ ሊነጠቅ የቻለው አጠቃላይና ጠንካራ የትግል ድርጅት ሳይኖረው በመቅረቱ ነው ። ሴረኞቹ ጥቂት መኮንኖች አስልጣን ኮርቻ ላይ ፊጥ ለማለት የቻሉት በዚህ ምክንያት ነው ። ይህ እውነት ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተገልጦአል ። ስለሆነም ከላይ እንደተባለው መሰረታዊ ለውጥ ሊመጣ

የሚችለው ሰፊው ሕዝብ በደንብ በአጠቃላይ ተደራጅቶ የሚመራው የራሱ የሆነ ከራሱ የወጣ ሰፊና ጠንካራ ተራማጅ ድርጅት ሲኖረው ብቻ ነው ። ያለበለዚያ ምርጦች ሲረኞች ለማጭበርበር እንደሚሞክሩት ያለምንም ድርጅት በጠመንጃና በሳንጃ በማስፈራራትና በፍራቢስ ፕሮፓጋንዳ በማወናበድ አይደለም ። ይህ ሆነ ብለው የሚፈጥሩት ውዥንብር አንድ ስንዝር እንኳን ወደፊት አያስኬድም፣ እንዲያውም እስካሁን የተደረገውንና የደረሰውን ስንመለከተው ወደ ሃላ ብዙ ኪሎሜትር ሄደናል ።

በጥቂት የተሸጡ መቆንኖች የሚመራው ወታደራዊው መንግስት የሰፊውን ሕዝብ መደራጀት እንደማይፈለግ ግልጽ ነው ። እንዲያውም አጥብቆ የሚቃወም መሆኑን በፋሽስታዊ ድርጊቶቹ በይፋ ገልጦአል ። ሰፊውን ሕዝብ አግልሉና በጨማው ስር ረግጠ የመንግስትን ስልጣን ለብቻው በሞኖፖል የያዘው ዲሞክራሲን አጥብቆ የሚያወግዘው ሰፊው ሕዝብ ጠንካራና አጠቃላይ የፖለቲካ ድርጅት እንዳያቆምና እውነተኛውን መሰረታዊ ለውጥ እንዳያመጣ ነው ። የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄና ፍላጐት ከምንም ሳይቆጥርና ትክክለኛውን መንገድ ትቶ ጠማማውን መንገድ በመምረጥ ወታደራዊ መንግስት ያቋቋሙ በጥቂት ራስ ወዳደች የሚመራው ደርግ ወደመሰረታዊ ለውጥ የገሰገሰውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለጊዜው ከማጨናገፍ በቀር ሌላ ምንም ፋይዳ ሊሰራ እንደማይችል የታወቀ ነው ። በምንም አይነት ከውድቀትና ከመውደም የሚያድነው የለም ። መሰረታዊ ለውጥ ግን ለጊዜው ቢዘገይም መምጣቱን ማንም ሊያስቀረው አይችለም ።

የሕዝቡ ቀዳማይ ጥያቄ ፊትም አሁንም ሕዝባዊ መንግስት ነው ። ይህም ለቅንጦት ሳይሆን መሰረታዊውን ለውጥ ለማምጣት ጠንካራና አጠቃላይ ድርጅት ለመመስረት ነው ። ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ሕዝቡ ሰባዊ መብቶቹንና ነፃነቶቹን ተጐናጽፎ በመደራጀት ባላባታዊ ስርአትንና ኢምፔሪያሊዝምን እንዲደመስስና እውነተኛውን ዲሞክራሲ እንዲመሰርት ያስችለዋል ። በምርጦቹ የሚመራው ደርግ ግን በማጭበርበር የቀድሞውን መንግስት ባለሟሎች የሰፊውን ሕዝብ ጠላቶች ከፍተኛ ቢሮክራቶችን መርጦ "የመማክርት ሸንጐ አቋቁሜላችሃለሁ" በማለት ዲሞክራሲን ዘቅዝቆ በመስቀል አፌዘበት ። በዲሞክራሲ ማፌዝና ሕዝቡ አይኑን አልከፈተም ብሎ መናቅ ራስን ከሁሉ በላይ በማድረግ መለኮታዊ ነኝ ማለት ለአጤ ሃይለስላሴ እንኳን እንዳልበጀውና በመዉረሸ ከውርደት አዘቅት ውስጥ እንደጣለው መገንዘብ እንዴት ያቅታል? ምርጦቹ ከዚህ ትንሽ ትምህርት እንኳን ለመቅሰም አለመቻላቸው ያስገርማል ።

ባሁኑ በኢትዮጵያችን ሁኔታ ድርጅትና ዲሞክራሲ የሚለያዩ ነገሮች አለመሆናቸው ግልጽ ነው ። ዲሞክራሲን መጠየቅና ለዲሞክራሲ መታገል ያስፈልጋል ። ማስፈለግ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው ። ሌላም ምርጫ ሌላው መንገድ ባርነት የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን እንዲሁም የፋሽዝምን የበዝባዥና የጭቆና ቀንበር ተሸክሞ ማቃሰት ነው ። ከሰላማዊው ሕዝብና ከወታደሩ በምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ተቋቁሞ ዋና ዋና የሕዝብ መብቶችንና ነፃነቶችን እንዲያስከብርና ስራ ላይ እንዲያውል ሁሉም አሞቱን ክስተር አድርጐ አስፈላጊውን መስዋእትነት ተቀብሎ መታገል መጋደል አለበት ። የሚያዋጣው መታገል መደራጀት መደራጀት ለከፍተኛ ትግል ለመሰረታዊ ለውጥ ከባዱንና መራራውን ትግል አሁኑኑ ወገብን ጠበቅ አድርጐ መጋተር ነው ። ይህ ብቻ ነው ዘለቄታ ያለው፣ ይህ ብቻ ነው የሚያዋጣው ።

እንግዲህ ባሁኑ ጊዜ ተራማጅ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ለምን ዲሞክራሲ ዲሞክራሲ የሕዝብ መንግስት የሕዝብ መንግስት እንደሚሉ፣ ከወታደሩና ከሰላማዊው ሕዝብ የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግስት እንዲቋቋም እንደሚፈልጉና ለዚህም እንደሚታገሉ ሳንዳንድ ሁኔታውን በደንብ ሳልተረዱና ተረድተው ደግሞ የግል ጥቅማቸውን በመፈለግ ለማወናበድ ለሚፈልጉ ሁሉ ግልጽ መሆን አለበት ።

ይህ ሁሉ የሚያስፈልገው ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ የተመለከተውን አይነት መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት መንገድ እንዲጠርግ ነው፣ ወደዚህ ግብ እንዲያቃርበን ነው፣ እውነተኛውን መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንድንችል ነው፣ ከሰፊው ሕዝብ አንዳንድ በሚገባ ያልነቁ ሕዝቦች የፖለቲካ ንቃታቸው የበለጠ ከፍ እንዲል ነው ።

ሆኖም አንዳንድ አድርባዮች የሰፊውን ሕዝብ ትግል ዋጋቢስ ለማድረግ ይሞክራሉ፣ የፋሽስቶቹ መሳሪያ በመሆን የሰፊውን ሕዝብ ግንባር ቀደም ታጋዮች ስልጣን ፈላጊዎች ናቸው በማለት ያወግዛሉ፣ ከሀደታቸውንና አወናባጅነታቸውን በማይጨበጡና በማይዳሰሱ ከንቱ ቃላት ለመሸፈን ይሞክራሉ፣ ግን እንደ ቢጤያቸቸው ከታሪክ ፍርድ አያመልጡም፣ አወናባጅነታቸው ይከሰትባቸዋል፣ የከሀደታቸውን ጽዋ ፉት ከማለት አያመልጡም፣ ስራ ለሰሪው እሾህ ለጣሪው ነውና ድርጊታቸውና ተንኮላቸው ያጋልጣቸዋል፣ አደናቀፍ ይጥላቸዋል ።

የእውነተኛ ተራማጆች የሃቀኛ የሕዝብ ወገኖች ቦታ ከሰፊው ሕዝብ ጐን ተሰልፍ ባለፈው የካቲት የፈነዳውን የትግል ቋያ ማፋፋም ነው፣ ለዲሞክራሲያዊው ትግል ለእውነተኛው ይሕዝብ መንግስት ትግል መደራጀትና ማደራጀት ነው ። በግንባር ቀደምትነት ሲታገሉ የቆዩትና አሁንም ይህንኑ ስፍራቸውን ይዘው የሚገኙት እርስበርሳቸው መፈላለግ አንድነታቸውን ማጠንከርና መደራጀት ይኖርባቸዋል ። ሰፊውንም ሕዝብ ለትግሉ መቀስቀስና ማደራጀት፣ የፖለቲካ ንቃቱ የበለጠ ከፍ እንዲል መካከሉ ገብተው አብረው እንዲሰለፉ ያስፈልጋል ። የረቮሉሽናውያን ታሪካዊ ስፍራ ሰፊው ሕዝብ መካከል ነው፣ የትግሉ ሜዳ እዚህ ነው ። የጊዜው ታሪካዊ ተግባራቸውም ከሰፊው ሕዝብ ጋር አብረው በመሰለፍና በመደራጀት ለዲሞክራሲ ለሕዝባዊ መንግስት የሚደረገውን ትግል ማንቀሳቀስና ከግቡ እንዲደርስ ማድረግ ነው ። የእውነተኛ ተራማጆችና ሪቮሉሽናውያን ስፍራ የሰፊው ሕዝብ የፊት ጀ ደጀን በመሆን ትግሉን ያለእንዳች ማወላወልና ወደ ኋላ ማለት መምራት ነው ።

ፊውዳሊዝም ፋሽዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይወድማሉ.-
ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋማል.
ዲሞክራሲ ያሸንፋል.
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።

## የበሬን ምስጋና አህያ ወሰደው

ወይም

## የወታደር አስተዳደር ደርግ

ፊት ከወጣ ጀርባ ሃላ የወጣ ቀንድ አዩኝ እንዲል
ጌሉቶ
ለታይ ለቆይ አለ ደርጉ ትናንት መጥቶ ::
ሕዝቡ በነቀለው በዚያ ጉቶ ፈንታ
ደርጉ ጉቶ ሆነ መቸ አለው ይሉኝታ ::
ሕዝቡ በነቀለው ባንዱ ጉቶ ፈንታ
መቶ ሃያ ጉቶ ተተክቶ እንዳፍታ
ያደና ቀረናል በወሬ ቱማታ ::
  አጤ ሃይሌ ቢሆን አርበኞች አሰዳጁ
  ደርጉም አለበዛነ በማደን በማፈን ያገሩን
  ተራማጁ፣
  ሁለቱ አንድ ናቸው አንዱ ያንዱ ቀዳጁ ::
ማሳውን ያረሰው ቀንበር ተሸክሞ
ፈሩን የቀደደው ቀንበር ተሸክሞ
ሂሳም ያበራዩ አውድማ ላይ ውሉ አፉን ተሸበበ
እንዲያ በድካሙ አለሙን መግቦ
የዚያን በሬ ትግል የበሬውን ልፋት የበሬን
ምስጋና
አህያ ነጠቀው ምርቱን ችሽከም አቤት ወሰደና ፈ:
ተማሪና ምሁር ወዝአደር ታጋይ
ባመነበት ፀንቶ ሳገሩ ለሕዝቡ እንዲያ ሲሰቃይ፣
ፊር እየቀደደ በፖለቲካ ማሳ
ምርቱን ያመረተው ሲወድቅ ሲነሳ፣
ትግሉ ተፋፍሞ አጤን ሲጥለው
ድንገት ደረሰና ከጥንት የነበረው ወታደር ፖሊሱ
ጄኔ ደጋፊው
ምርቱን ወሰደና
ፊቱን አዞረና
ጀርባውን ሰጠና
ደርግ በሚል ስያሜ ራሱን ሸመና
ባጤ ባደ መንበር ቁጭ ቂብብ አለና
አመስግኑኝ አለ በሌሎች ምስጋና ::
  ዛሬ ለወጉ አሁን ለወጉ
  በመንግስት ስም በሃገራችን ይገኛል ደርጉ ::
  ደርጉ ደረሰ ደርጉ ደረሰ
  እነሆኝ ድርቅ ይል ቀን ባስ ::
አጤ ቢሄድ ጊዜ በፊትበ በር ገባና
ተተካ በቦታው በስር ቁሽ በር ገብቶ ደርጉ
አጤን ሆነና ::

ባጤ ሃይሌ ጊዜ አፈሙዝ ደቀና በተማሪ ላይ
ባጤ ሃይሌ ጊዜ አፈሙዝ ደቀና በወዝደር ላይ
ባጤ ሃይሌ ጊዜ አፈሙዝ ደቀና በተራማጁ ላይ
የፈጀው ጩፍጭፍ ሁሉን ያደረገው የጥይት ሲሳይ
አመስግኑኝ ባዩ ደርጉ አይደለም ወይ?

ተመዞ የነበር የወታደር ሳንጃ በተማሪ ላይ
ተመዞ የነበር የወታደር ሳንጃ በወዝአደር ላይ
ተመዞ የነበር የወታደር ሳንጃ በተራማጁ ላይ
እንደተመዘዘ አሁንም ስናይ
ምን እንበለው ደርጉን ባሰየው ጠባይ?

ለካ እንዳጤ ሃይሌ ተማሪ ገደለ
ለካ እንዳጤ ሃይሌ ወዝአደር ገደለ
ለካ እንዳጤ ሃይሌ ተራማጁ ገደለ
ገና በጅምሩ በደም ተነከረ በደም ተበከለ ::
እምን ላይ ነው ብሉ ተራማጅነቱ
እምን ላይ ነው ብሉ ተቆርቋሪነቱ
እምን ላይ ነው ብሉ የሰው ልጅነቱ
ስልጣን ከመያዙ ሰው ጥዳ ማለቱ ::
ለካ እንዳጤ መንግስት በደም ሃይል ተፀንሶ
ተፋጥኖ የመጣው ደርጉ እንዲያ ገስግሶ
ለካ ለማፈን ነው ተራማጁን ሁሉ ወዝአደሩን
ሁሉ በጥይት ጨርሶ ::
ባሰሳ የመጣ ይጠፋል ባሰሳ
ደርጉ ሳገር ሳይሆን ባገር ላይ ተነሳ ::
  አጤ ሃይሌ ቢሆን አርበኞች አሰዳጁ
  ደርጉም አለበዛነ በማደን በማፈን ያገሩን
  ተራማጁ፣
  ሁለቱ አንድ ናቸው አንዱ ያንዱ ቀዳጁ ::
ሰገሌ ተፈሪንበወሉ ደም ወለዳ
ከሃምሳ አመት በላይ አስረፈጀች ኢትዮጵያን በግፍ
አስጠምዳ ::
አዲሳባም ደርጉን በወሉ ድርቅ ወለዳ
ይኸው ጀምራለች ኢትዮጵያን ለታወድም በሃይል
አስጠምዳ ::

በመሃል ሰፋሪ አስታካ ፏፈሪ ያቸ ትንሽ ኩዛ
ከሃምሳ አመት በላይ ፈላጭ ቆራጭ ሆነች ሃበሻን
ስትገዛ ።
የተፈሪ መንግስት ትናንትና አከትሞ
አሱን የመሰለ ተተካ ፈጽሞ ።

በተማሪ ትግል አያ ደርግ አስታከ
በወዝአደር ትግል አያ ደርግ አስታከ
በተራማጅ ትግል አያ ደርግ አስታከ
ፈላጭ ቆራጭ ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰበከ ።
ለመሳፍንት ባስቴ ወታደር ገዳይ
ለመኳንንት አዝኖ ወዝአደር ገዳይ
ፍርድ አዋቂ ዳኛ ፍትህ አጿሳዳይ
አሁን የት ይገኛል ይህን ደርግ መሳይ.
አሁን አንደደርጉ አስተዋይ ማን አለ
አሁን አንደደርጉ ብልህስ ማን አለ
ለመኳንንት አዝኖ፣ ለመሳፍንት ባስቴ፣ ደም
አይፍሰስ የሚል ድሃ አየገደለ ።
ደርጉ ተራቀቀ
በጥበብ ጠለቀ
በአስምሮ ደርጅቶ በአውቀት ጉላመሰ
ደም አይፍሰስ ይላል ደም አፏፈሰሰ ።
ዛሬ ለወጉ አሁን ለወጉ
በመንግስት ስም በሃገራችን ይገኛል ደርጉ ።
ደርጉ ደረሰ ደርጉ ደረሰ
እነሆኝ ደርቀ ይልቀን ባሰ ።

ካምስት አመት ሸሸት አጤ ተመልሶ
አርበኛውን ፈጀው ባንዳን አቅፍ ለብሶ፣
ደርጉም ስልጣን ሲይዝ ባጤ ስፍራ ገብቶ
ያጤን ስልጣን ቀምሶ፣
ተራማጅ ለማፈን ያጤን ወንጀለኞች ሸማቸው
መልሶ ።
ስልጣን ከመያዙ ወዲያው ተሯሯጦ
ደርጉ አጤን ሂነብን በገብሩ ፈጽሞ ።
ያደገበን አመራር አርጉት እንደዋዛ
ደርጉ ቀጡን አጣ ድንፋታው ተንዛዛ ።
ከሃይለስላሴ የባሰ መሃይምን የባሰ ደንቆሮ
የታሪክን ጉዞ ሊያቆም በሃይል አስሮ፣
ያበዩቱን ትግል ሊያስቀር አስፈራርቶ
አሊያም በሸንገላ
የሚቃከረው ደርግ ይህ አደራበሰ፣
ማን በነገረልን ማን ባስተማረው
የድሃሪያች ሸንጐ ደርጉ ቢገባው፣
እንደማይችል ማንም ያበዩትን ትግል
የታሪክን ጉዞ
መቼም ለማስቀረት ሳንኛ ሸተሉ መዞ ።

በአዋጅ ፈቀቅ አይልም በጉራ አይካሄድም
በደርግ ማዘዝ
አብዩት ሰርግ አይደል ወይም የራት ግብዣ ።
ታሪክ መንገዱ አለው አብዮትም ህግ፣
እንኳን አንድ ቁርቶ አስር ሃያ ደርግ
ቢቋቋም ቢሰራ እንዲያው ያለቀጥ
የታሪክን መንገድ የአብዩትን መንገድ
አይችል መለወጥ ።
አጤ ሃይሌ ቢሆን አርበኞች አሳዳጅ
ደርጉም አለበዚህ በማደን በማፈን
ያገረን ተራማጅ፣
ሁለቱ አንድ ናቸው የደበሉ ቀዳጅ ።

---

## አጨጭር የትግል ዜናዎች

### 4ኛ ዙር ሊያደርጉ ነው እንዴ?

3ኛ ክፍለጦር 25ኛ ሻለቃ ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔንና ሌሎች መኮንኖችን የንኡስ ደርጉን አባሎችና የአብዩ ደርጉን መልእክተኞች አሰሩ ። የሚጠይቁት የ7 ብር ጭማሪ መሆኑ ተሰምቶአል ። የሰሜኑ ንኡስ ደርግ የአብዩ ደርጉን በላይነት አለመቀበሉን አሰምቶአል ። የፖሊስ ሰራዊቱም በጊታቸው በኮሎኔል በላቸው ጀማነህ መሪነት ከደርጉ ገሸሽ በማለት ላይ ይገኛል ። 5ኛ ክፍለጦር እየተባለ የሚጠራው የመሃንዲስ የአርሚ አቪሽን ወዘተ. ሰራዊት ለደርጉ ድጋፉን ከከለከለ ሰንብቶአል ። እንዲሁም በጆቄር ወለድ በታንከኛ ጦር ውስጥ በልዩ ልዩ ግጭቶች የተነሳ ብዙ ወታደሮች ታስረዋል ። የ4ኛ

ከፍለጦርና የከበርዘበኛውም ባለሌላ ማእረግ ሕዝቡ በወታደር ላይ በሚያሳየው ጥላቻ ግር ብሎት የደርጉን ነገር ቸላ ብሎታል ። በጠቅላላው ነገሩ ሲታይ ለ3ኛው ዙር የተደረገውን እንቅስቃሴ ይመስላል ። ልዩነቱ ግን ከዚያን ጊዜ ይበልጥ አድሃሪ ሃይሎች መዘጋጀታቸውና አብዮታኞችን ለማጥፋት መቁረጣቸው ነው ። ደርጉ በማመንታቱ በመዝረክረኩ አላስደሰታቸውም፣ አንዳንድ የደርጉ ፕሮፓጋንዳም አልጣማቸውም ። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶችም ደርጉ ውስጥ ያሉአቸው ቡችሎች ደርጉን በትነው ስልጣን መያዝ ባለመቻላቸው ቅር ተሰኝተዋል ። እንግዲህ 4ኛውን ዙር እነርሱም ይፈልጋሉ ማለት ነው ። ከሚኒስትሮች እነበላቸው ጀማነህ እነተካልኝ እነሸመልስ እንዲሁም አንዳንድ ቴክኖክራቶችና የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች በሴራው ውስጥ እንዳሉበት ይገመታል ። በጠቅላላው ጊዜው አመቺ ስለመሰላቸው አሜሪካኖችና ቡችሎቻቸው ደርጉን ጥለው ጁንታ ለማቋቋም ተነስተዋል፣ 4ኛው ዙር የነርሱ ይመስላል ። ከታሪክ ምንም ጊዜ የማይማሩት አድሃሪዎች የሕዝብን ቸገር በማባባስ መቃብራቸውን እንደሚቆፍሩ አልተረዱም ።

<u>የገጠሩ ሕዝብ ትግል ተስፋፍቶአል ።</u>

በሆሮጉድሩና በዉሊሶ ወረዳ ሕዝቡ ተነሳስቶ ለብሄሮች እኩልነትና መሬት ለአራሹ በማለት ትጥቃዊ ትግል ጀምሮአል ። እንዲሁም በሰላሌ አውራጃ በሚካሄደው ትግል ለጊዜው ከሕዝብ ወገን አራቱ ሰዎች ቢያዙና የሁለቱ — የአቶ ጣፋ ሰኚና የአቶ ሊሜንሶ ወዳጆ — ንብረት በወታደራዊው መንግስት ቢዘረፍም ትግሉ ቀጥሎአል ።

<u>ያለአግባብ መበልፀግና ደርጉ:</u>

የደርግ አባሎች በየቦታው ሲዘዋወሩ በቀን 25 ብር አበል ያገኛሉ ። እንዲሁም ከባለ ስልጣኖች የተወረሱትን መኪናዎች ተከፋፍለው ታርጋቸውን ለውጠው ከተማ ውስጥ ሲዘዋወሩባቸው ይታያሉ ።

<u>የስድስት ሰዎች መገደል</u>:

ከሻሸመኔ ወደወላሞ ሰደ መንገድ ላይ ስድስት የሃብታም ገበሬ ተቀጣሪዎች መሬታቸውን በተቀሙ ጭሰኞች ተገደሉ ።

<u>የመለካሴዴ ሰራተኞች፤</u>

የኑሮን መወደድ በመጠኑም ቢሆን ለመቋቋም የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው ጠይቀው እምቢ የተባሉት የመለካሴዴ ሰራተኞች በጥቂት ቀናት በፊት ጀምሮ ስራ አቁመው ነበር ። በዚህም ምክንያት በመለካሴዴ የእርሻ ጣቢያ የሰፈረው በመቶ አለቃ አያሌው የሚመራ ፖሊስ የምንሰራ ማቆም ነው እናንተ ወመኔዎች እያለ ቀኑን ሙሉ በጉልበታቸው ሲያስቀምጣቸውና ጺ በንብርክክ ሲያስኬዳቸው ውሎአል ። እንዲህ ነው ይሕዝብ ወገን የሆነ ወታደር. እንዲህ ነው የሕዝብ ወገን የሆነ ደርግ.